# ተወኝ

ላታስታምም አትመመኝ
ላትወስደኝ አታንጠልጥለኝ
ይቅር፡አንጀቴን ቁረጠኝ
ጋሽዬ፡አልወድሽም በለኝ
እጅ እጅ አልበል አታባክነኝ
ባክህ፡ወንድ ነው ቆራጡ፡እንትፍ እርግፍ አርገህ ተወኝ
አየህ፡እንዳንተ አባት አለኝ
ሴት በወለድኩ ተዋረድኩ፡ረከስኩ፡ቀለልኩ እሚለኝ
እኔም እንዳንተ እህት አለኝ
ስጋሽን ሳይሆን ልብሽን፡ከፍተሽ ጥለሽ እምትለኝ
እና ተወኝ፡ባክህ ተወኝ
አንዳንተ እኔም አለኝ እናት
የሴት ቁንጮ እምመስላት
ጎረቤት ፊት እምታፍር፡እንዲህ ሆነችልሽ ሲሏት!...
እና አልሆንሽም በለኝ
ባክህ አንጀቴን ቁረጠኝ...
ፍቅር እንደሁ የኔ ይበቃል፡ላንተም ለኔም እኔው ልውደድ
ከዘመድ ግንባር ደብቄ፡እኔ ብቻዬን ልንደድ
ብቻ፡ከወጥመድህ ለየኝ
አልችልህም፡ንቀህ ማረኝ
ካንተም፡ከስሜም ከቤቴም፡ያጣሁ ብኩን አታድርገኝ
ባክህ፡አንጀቴን ቁረጠኝ
ተወኝ፡ተወኝ፡ተወኝ።

ጸጋዬ ገ/መድህን

፲፱፻፺፯ - ኒው-ዮርክ

# ተወኝ

ላታስታምም አትመመኝ
ላትወስደኝ አታንጠልጥለኝ
ይቅር፡አንጀቴን ቁረጠኝ
ጋሽዬ፡አልወድሽም በለኝ
እጅ እጅ አልበል አታባክነኝ
ባክህ፡ወንድ ነው ቆራጡ፡እንትፍ እርግፍ አርገህ ተወኝ
አየህ፡እንዳንተ አባት አለኝ
ሴት በወለድኩ ተዋረድኩ፡ረከስኩ፡ቀለልኩ እሚለኝ
እኔም እንዳንተ እህት አለኝ
ስጋሽን ሳይሆን ልብሽን፡ከፍተሽ ጥለሽ እምትለኝ
እና ተወኝ፡ባክህ ተወኝ
አንዳንተ እኔም አለኝ እናት
የሴት ቁንጮ እምመስላት
ጎረቤት ፊት እምታፍር፡እንዲህ ሆነችልሽ ሲሏት!...
እና አልሆንሽም በለኝ
ባክህ አንጀቴን ቁረጠኝ...
ፍቅር እንደሁ የኔ ይበቃል፡ላንተም ለኔም እኔው ልውደድ
ከዘመድ ግንባር ደብቄ፡እኔ ብቻዬን ልንደድ
ብቻ፡ከወጥመድህ ለየኝ
አልችልህም፡ንቀህ ማረኝ
ካንተም፡ከስሜም ከቤቴም፡ያጣሁ ብኩን አታድርገኝ
ባክህ፡አንጀቴን ቁረጠኝ
ተወኝ፡ተወኝ፡ተወኝ።

ጸጋዬ ገ/መድህን

፲፱፻፺፯ - ኒው-ዮርክ